

# የምድረ በዳው ጉዞ

ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ ምድር ሲወጡ መራቸው።

* እግዚአብሔር ለሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ እንዲያወጣቸው ትዕዛዝ ሲሰጠው በቀን በደመና በሌሊት ደግሞ በእሳት አምድ ይመራቸው ነበር።

* ሆኖም ፈርኦን እስራኤላውያንን በመልቀቁ ተፀፀተ። በቀይ ባህር ዳርቻ ላይም ደረሰባቸው። እግዚአብሔርም ባህሩን በመክፈል የሚያልፉበትን ደረቅ ምድር ለእስራኤላውያን አዘጋጀላቸው። እነርሱም ውሃ እንደግድግዳ በቀኝና በግራ ቆሞ እያዩ በደረቅ ምድር ባህሩን ተሻገሩ። ሆኖም ግብፃውያን እንደእስራኤላውያን ለመሻገር ሲሞክሩ በባህር ውስጥ ሰጥመው ቀሩ። እስራኤላውያን ግን ዳኑ።

* እስራኤላውያን ከዚህ ተአምር በኋላ በምድረ በዳ እየተጓዙ እያሉ ስለምግብ በእግዚአብሔር ላይ አጉረመረሙ። ስለዚህ እግዚአብሔር ምግብ ሰጣቸው። እግዚአብሔር በማለዳ የዳቦ ቁርስራሽ የመሰለ ምግብ ከሰማይ ላከላቸው። እነርሱም መና ብለው ጠሩት። በየእለቱም ሕዝቡ ለአንድ ቀን የሚበቃ መና ይሰበስቡ ነበር። እግዚአብሔርም በየቀኑ መናን ይልክላቸው ነበር። ሥጋ በጠየቁ ጊዜም እግዚአብሔር ድርጭቶችን ላከላቸው። ስለዚህ እነኝህን አእዋፍ በመያዝ ስጋ መብላት ቻሉ።

* አንድ ወቅት ላይ እስራኤላውያን ምንም ውኃ በማይገኝበት ምድረ በዳ ላይ ደረሱ። በሙሴ ላይም አጉረመረሙ። ሕዝቡና ከብቶቻቸው በሙሉ ኃይለኛ ውኃ ጥም ያዛቸው። ሙሴም እግዚአብሔርን ምን ማድረግ

እንደሚገባው ጠየቀው። እግዚአብሔርም በያዘው በትር ውኃውን እንዲመታው አዘዘው። ሙሴም ይህን ሲያደርግ በጣም ብዙ ውኃ ፈለቀ። ሕዝቡም የሚፈልጉትን ያህል ውኃ አገኙ። ጠጥተውም ረኩ።

ይህን የእስራኤላውያንን ከግብፅ ምድር መውጣት ታሪክ በመፅሀፍ ቅዱስ በዘፀአት ምዕራፍ 14 – 16 ባለው ክፍል ውስጥ ማግኘት ይቻላል።

http://gardenofpraise.com